MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

# የወላጅ/የሞግዚት መመሪያ

## ለ ሰክሽን 504 የተሐድሶ ደንብ 1973

### ሰክሽን 504 ምንድነው?

ሰክሽን 504 የተሐድሶ ማቋቋም 1973 (ሰክሽን 504) ማለት አካለስንክልና ያለባቸውን ዜጎችን መብት የሚያስጠብቅ የፌደራል ደንብ/ህግ ነው። ህጉ/ደንቡ ማናቸውም የፌደራል ገንዘብ የሚያገኙ ድርጅቶች ብቃት ያላቸውን ግለሰቦች በአካል ስንክልና ምክንያት አድልዎ እንዳይደረግባቸው ይከለክላል። ጠቅላላ የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች በሰክሽን 504 መሰረት ተግባራዊ መደረግ አለባቸው።

የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ/Regulation ACG-RB በሰክሽን 504 የተሐድሶ ደንብ 1973 ለሚታቀፉ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ያለችግር የሚገለገሉበትን/Accommodations እና መጠነኛ ለውጥ-ማሻሻል ለተማሪዎች ስለ ሰክሽን 504 አፈጻጸም የ MCPSን ሂደት ይገልጻል። በድረ-ገጽ ላይ ቅጂዎች ይገኛሉ።

### ብቃት ያለው ማነው?

የአካል ስንክልና ያለባቸው ተማሪዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን በአጠቃላይ/በወሳኝነት የሚገድብ የአካል ወይም የአእምሮ ድክመት/ስንኩልነት ካለባቸው ለማቋቋም በሰክሽን 504 መታቀፍ ይኖርባቸዋል። ሰክሽን 504 ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን የሚገልጸው "ራስን መንከባከብ፣ በሰው ጉልበት/በእጅ የሚሠሩ ሥራዎችን፣ ለመራመድ፣ ለማየት፣ ለመስማት፣ ለመናገር፣ ለመተንፈስ፣ ለመማር፣ ለመሥራት፣ ለመቆም፣ እቃ ለማንሳት፣ ለማጎንበስ፣ ለማንበብ፣ ለማስተዋል/ለትኩረት፣ ለማሰብ፣ እና ለመገናኘት" ተግባራት በሚል ነዉ። ተማሪው/ዋ ባለበ(ባ)ት ስንክልና ምክንያ ከአንድ በላይ ዋነኛ የህይወት እንቅስቃሴዎች ላይ እንድምታ ሊኖረው ይችላል።

የአካል ስንክልና በምርመራ መገኘቱ/መታወቁ አንድን ተማሪ ወዲያውኑ/ባንዳፍታ ለሰክሽን 504 ብቁ ሊያደርገው/ሊያደርጋት አይችልም። መምህራን ወይም ወላጆች/ሞግዚቶች ተማሪው/ዋ ለሰክሽን 504 ብቁ ይሆናል የሚል ስሜት ካደረባቸው፣ የሰክሽን 504 ቡድንን በልጁ(በልጅቱ) ት/ቤት ስብሰባ እንዲያደርግ ለመጠየቅ ይችላሉ። ቡድኑ የሚያካትተው የት/ቤት ሠራተኞችን፣ ሌሎች ስፔሻሊስቶችን፣ ወላጆች/ሞግዚቶችን፣ እና አስፈላጊ ከሆነ ተማሪውን ጭምር ነው። ቡድኑ ከበርካታ ምንጮች ያገኛቸውን መረጃዎች/ኢንፎርሚሽን (ለምሳሌ፡- ሪፖርት ካርዶችን፣ ምርመራ የተደረገባቸውን፣ የሜዲካል ሪፖርቶችን፣ እና ሌሎች መረጃዎችን) ተማሪው/ዋ ለሰክሽን 504 ብቃት እንዳለው/እንዳላት ለመወሰን ይገመግማል። በሰክሽን 504 የታቀፉ ሁሉም ተማሪዎች መገልገያ/አኮሞዴሽን አያስፈልጋቸውም ይሆናል። ተማሪው/ዋ በእኩልነት በትምህርት ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍ/የመማር እድል እንዲኖረው/እንዲኖራት ለማስቻል መጠቀሚያ መሣሪያዎች ያስፈልጉ(ጓ)ት እንደሆነ ለመወሰን ቡድኑ የተማሪው(ዋ)ን አሠራር/አፈጻጸም ስንክልና ከሌላቸው ጓደኞች/እኵዮች ጋር ማመዛዘን/ማስተያየት አለበት። ቡድኑ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት አንዳንድ ሁነቶች ስንክልና ከሌለባቸው እኩዮች ጋር ሲመዛዘን፣ ተማሪው(ዋ)

- የት/ቤትን ሥራ ለማከናወን በተከታታይ ብዙ ጊዜ ይፈጅበታል/ይፈጅባታል፣
- የት/ቤት ሥራ ለውጥ እንዲደረግለ(ላ)ት ሁልጊዜ ይፈልጋል/ትፈልጋለች፣
- ብዙውን ጊዜ የትምህርት መርሃ ግብር ተደራሽነትን የሚያደናቅፍ ባህሪ ያሳያል/ታሳያለች፣እና
- ራሱ(ሷ)ን ለመርዳት እገዛ ያስፈልገዋል/ያስፈልጋላታል።

### የሰክሽን 504 እቅድ ምንድነው?

ተማሪ /ዋ ለሰክሽን 504 አስፈላጊ ነገሮች መመሪያዎችን የማሟላት ብቃት ካለው/ካላት፣ ተማሪው/ዋ በት/ቤት የሚጠቀምበት/የምትጠቀምበት አስፈላጊ ነገሮችን የሰክሽን 504 እቅድ ይዘጋጃል። እቅዱ የስንክልናውን ዓይነት/ሁኔታ በመግለጽ፣ በስንክልና ምክንያት የሚያስከትለው የህይወት እንቅስቃሴ ስንክልና፣ የተማሪው(ዋ)ን ፍላጎት ለማሳካት መሟላት ያለባቸውን አስፈላጊ ገሮች፣ እና አስፈላጊ ነገሮች፣ እና አስፈላጊዎቹን ነገሮች ለመተግበር ኃላፊነት ያለበ(ባ)ት ሰው/ሰዎች።

የሰክሽን 504 እቅድን ማዳበር የት/ቤት ኃላፊነት ነው። ነገር ግን፣ ወላጆች/ሞግዚቶች የሰክሽን 504 አይነተኛ የቡድን አካል ስለሆኑ እቁዱ በሚሠራበት ወቅት አብረው መጨመር/መሳተፍ አለባቸው። አስፈላጊ ሲሆን ተማሪው/ዋ መጨመር አለበ(ባ)ት። ከእርስዎ ተማሪ ጋር በቀጥታ ለሚሠሩ መምህራን ስለ ፕላን የሚያሳውቅና የሚያስተባብር/የምታስተባብር፣ በየዓመቱ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ግምገማ የሚያደርግ/የምታደርግ ኬዝ-ማናጀር ይመደባል/ትመደባለች። ለሰክሽን 504 እቅዶች MCPS የመገናኛ አውታር መድረክ/እቅድ ይጠቀማል።

### የኔ የወላጅነት መብቶች ምንድናቸው?

ወላጆች/ሞግዚቶች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፡-

- ተማሪያቸው በስንክልና ምክንያት ምንም አድልዎ ሳይደረግበ(ባ)ት በህዝባዊ የትምህርት ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ ተጠቃሚ ለመሆን መቻል።
- ተማሪያቸውን የሚመለከቱ የማንነት መለያ፣ ግምገማ፣ እና/ወይም እንዲሟላለት/እንዲሟላላት የተባሉትን መጠቀሚያ ነገሮች ማሳወቅ።
- ተማሪያቸው ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት በነፃ እንዲያገኝ/እንድታገኝ። ይህ የሚጨምረው/የሚያካትተዉ በተቻለ መጠን ስንክልና ከሌላቸው ተማሪዎች ጋር በተገቢ ሁኔታ እኩል ትምህርት የማግኘት መብትን ነዉ።
- ተማሪያቸው ስንክልና ከሌላቸው ተማሪዎች እኩል በት/ቤት ፕሮግራሞች እና ከከሪኩለም ውጪ በት/ቤት የሚደገፉ እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍ እድል እንዲኖረው/እንዲኖራት።
- የተማሪያቸውን የትምህርት ሪኮርድ/መረጃዎችን የመመርመር እና ቅጂ የማግኘት።
- የማንነት መለያ፣ ግምገማ፣ እና የምደባ/ፕሮግራም ከተለያዩ ምንጮች በተገኙ መረጃዎች እና የተማሪው(ዋ)ን ፍላጎት ከሚያውቁ ሰዎች በተገኘ ኢንፎርሜሽን መሠረት የተሰጠ ውሳኔ፣ ግምገማው ምን ማለት እንደሆነና ስለ ምደባ ያሉትን አማራጮች።
- ስለ ተማሪያቸው መለያ፣ ስለ ግምገማ፣ ወይም ምደባ/ፕሮግራም ውሳኔው ካላረካቸው ስለ ጉዳዩ መፍትሔ የመሻት መብት አላቸው።

የ MCPS ቅሬታ አጣሪ እና ውሳኔ ሰጪ ክፍል, 850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, Maryland 20850, በMCPS ሰክሽን 504 ላይ የሚከሰቱ ቅሬታዎችን የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት። ቤተሰብ/ሞግዚቶች ሰክሽን 504 ውሳኔዎች ይግባኝ ለማለት የ MCPS ሰክሽን 504 አስተባባሪን በስልክ ቁጥር 301-517-5864 ለማግኘት ይችላሉ። የ MCPS ብሮሹር/በራሪ ጽሑፍ ቅጂ፣በሂደት ላይ ያለውን መረጃ የመጠበቅ/መከላከል፡- ሰክሽን 504 የመልሶ ማቋቋም ደንብ 1973ስለ ሰክሽን 504 የበለጠ ዝርዝር መረጃ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

## ስለ ሰክሽን 504 የበለጠ ለማወቅ/ለመማር የምችለው የት ነው?

ስለ ሰክሽን 504 እና አስፈላጊ ነገሮች/accommodations በርካታ መረጃዎችን ከሚከተሉት ምንጮች ለማግኘት ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| በት/ቤት ከሚገኝ/ከምትገኝ የሰክሽን 504 አስተባባሪ | |
| ከ MCPS የሰክሽን 504 አስተባባሪ | 301-517-5864 |
| የ MCPS የቅሬታ ውሳኔ ሰጪ ክፍል<br>www.montgomeryschoolsmd.org/departments/special-education/compliance/section-504.aspx | 301-517-5864 |
| በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የዜጎች መብቶች ጽ/ቤት<br>http://wdcrobcolp01.ed.gov/CFAPPS/OCR/contactus.cfm | 215-656-8541<br>1-800-421-3481 |

# የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የ ፀረ-መድሎ መግለጫ

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) በዘር፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በዝርያ፣ በትውልድ ሃረግ፣ በዜግነት፣ በኃይማኖት፣ የፍልሰት አቋም/ይዞት፣ በጾታ፣ በጾታ ልዩነት፣ በጾታ ማንነት መገለጫ፣ የጾታ ባሕርያት፣ በጾታ ግንኙነት፣ በቤተሰብ ይዞታ/አቋም፣ በጋብቻ፣ በእድሜ፣ በሰውነት ወይም በአእምሮ ጉዳተኝነት፣ በድኽነት፣ በማሕበራዊና ኤኮኖሚያዊ አቋም፣ በቋንቋ፣ ወይም ሌላ በሕግ እና በሕገ መንግስት የታቀቡ ሕውነቶችን መሠረት ያደረገ ህገ-ወጥ መድልዎን ይከለክላል። መድሎ/ልዩነት የሕብረተሰባችንን በራስ የመተማመን፣ የእኩልነትን መንፈስ ለመፍጠር፣ ለማዳበርና ለመደገፍ እየተደረገ ያለውን የቆየ ልማድ/ጥረት ይሸረሽራል/ያዳክማል። ልዩነት/መድሎአዊነት የሚከተሉትን ጥቂት ምሳሌዎችን ያካትታል፡- ጥላቻ፣ ሁከት/ረብሻ፣ ደንታቢስነት፣ ትንኮሳ፣ ጉልበተኝነት/ወከባ፣ ንቀት፣ ብቀላ/የበቀል ርምጃ፡፡ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የሞንጎሞሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድን መርህ/ፖሊሲ ይመልከቱ (ACA), የእኩልነት፣ ሚዛናዊነት/የፍትሕ ባህልን ማዳበር፡፡ ይህ መርህ/ፖሊሲ የቦርዱን እምነት የእያንዳንዱ ተማሪ ብቃትና ተፈላጊነት በተለይም የትምህርት ውጤት በግለሰብ ሁኔታ የተሞረኮዞ በሚል አስተሳሰብ/ትንበያ መሆን እንደሌለበት ያረጋግጣል። መርሁ/ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህን/እኩልነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎችን የተዛባ ስውር አመለካከት፣ ጭቦኛ/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግ፣ በተቋማት መዋቅሮች ላይ የሚፈጸሙ መሰናክሎች፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል።

| በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች ሠራተኛ ላይ መድሎ/የማዳላት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ካለዎ* | በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች ተማሪዎች ላይ መድሎ/የማዳላት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ካለዎ* |
|---|---|
| የሰራተኞች አገልግሎት እና ግንኙነት ጽ/ቤት<br>የአፈጻጸም እና ክትትል መምሪያ/ዲፓርትመንት<br>አድራሻ፡- 850 Hungerford Drive, Room 55<br>Rockville, MD 20850<br>የስልክ ቁጥር፡ 240-314-4899<br>OCOO-EmployeeEngagement@mcpsmd.org | የት/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት<br>የት/ቤት አስተዳደርና አፈጻጸም-ትግበራ ቡድን<br>አድራሻ፡- 850 Hungerford Drive, Room 162<br>Rockville, MD 20850<br>ስልክ፡- 301-279-3444<br>OSSI-SchoolAdministration@mcpsmd.org |

* ምርመራ/ክትትል እንዲደረግ የአካል ጉዳተኛ ስለ ሆኑ ተማሪዎች መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎችን በሚመለከት (accommodations) የሚቀርቡ ጥያቄዎች፣ ክሶች፣ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች ወደ "የልዩ ትምህርት አፈጻጸም ቁጥጥርና ውሳኔ ሰጭ ጽ/ቤት" (Office of Special Education, Resolution and Compliance Unit), at 301-517-5864. ሊቀርብ ይችላል። ለሠራተኞች መዘጋጀት ወይም መሻሻል ያለባቸውን ነገሮች በሚመለከት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ወደ ሠራተኛ አገግሎት እና የስራ ግንኙነት የቅሬታና ክትትል ጽ/ቤት (Office of Employee Engagement and Labor Relations, Department of Compliance and Investigations), ስልክ፡- 240-314-4899 ሊቀርብ ይችላል። በተጨማሪም መድሎ/አድልዖ ቅሬታ ለማሰማት ለሌሎች ድርጅቶች/ኤጀንሲዎች፤ ለምሳሌ የዩ.ኤስ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የስራ እድል ኮሚሽን (U.S. Equal Employment Opportunity Commission, Baltimore Field Office, City Crescent Bldg., 10 S. Howard Street, Third Floor, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);ወይም ዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት የሰብአዊ መብት ጽ/ቤት U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Lyndon Baines Johnson Dept. of Education Bldg., 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-1100, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html ለማቅረብ ይቻላል።

ይህን ሰነድ ከእንግሊዝኛ በሌሎች ቋንቋዎች የውሂብ-ሕትመት ቅርጽ በአካል ጉዳተኝነት የሚኖሩ አሜሪካኖች ህግ በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች - የሕዝብ ማስታወቂያ ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፡- 301-279-3853፤ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org. በጥየቃ ለማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚፈልጉ ወይም በምልክት የተዘጋጀ ትርጉም ለሚያስፈልጋቸው፤ በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን Office of Interpreting Services በስልክ ቁጥር፡- 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) ወይም Interpreting_Services@mcpsmd.org.መጠየቅ ይቻላል። የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፤ ወጣት ወንድ/ሴት ስካውቶችን እና ሌሎችም የሚመለከታቸውን ወጣት ቡድኖችን በእኩል ያስተናግዳቸዋል።

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

Rockville, Maryland

ሕትመት፡- በማቴሪያሎች ማኔጅመንት ለቅሬታ ውሳኔ ሰጪ ክፍል
ትርጉም፡- በቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶች ክፍል • የኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት

Language Assistance Services Unit • Office of Communications

0122.18ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 7/17 • NP